የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፰
አዲስ አበባ ሀምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No 38
ADDIS ABABA 15th July, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷/፪ሺ፲፫

የተባበሩት መንግሥታት የመንገድ ትራፊክ ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ……………….…ገጽ ፲፫ሺ፬፻፸

## Content

Proclamation No.1260/2021

Proclamation for the Ratification of United Nations Convention on Road Traffic....Page 13470

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷/፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**የተባበሩት መንግሥታት የመንገድ ትራፊክ ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

የተባበሩት መንግሥታት የመንገድ ትራፊክ ኮንቬንሽን በኦስትሪያ /ቪየና/ እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር ፯ እስከ ኖቬምበር ፰ ቀን ፲፱፻፷፰ ድረስ በተደረገው ውይይት በተሳታፊ አባል ሀገራት የጋራ ውሳኔ ጸድቆ ስራ ላይ የዋለ በመሆኑ፤

ስምምነቱ ዓለም አቀፍ የመንገድ ትራፊክን በሚመለከት የተጠቃለለና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የያዘ በመሆኑ፤

ኢትዮጵያ ሀገራችን የባህር በር የሌላት በመሆኗ የመንገድ ትራፊክ ሕጎቿን ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማጣጣም ወደ ሌሎች በተለይም ወደ ጎረቤት ሀገራት የሚደረግን እንቅስቃሴ ቀላልና ቀልጣፋ ለማድረግ እና በሀገራችን ያለውን የመንገድ ደህንነት ከፍ ወዳለ ደረጃ በማሳደግ በመንገድ ትራፊክ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ስምምነቱ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ስለታመነበት፤

**PROCLAMATION NO.1260 /2021**

**PROCLAMATION FOR THE RATIFICATION OF UNITED NATIONS CONVENTION ON ROAD TRAFFIC**

**WHEREAS,** the United Nations Convention on Road Traffic was adopted in Austria, /Vienna/, by member states attending the meeting held from October 7 to November 8, 1968; and has been in force;

**WHEREAS,** the Convention has consolidated and internationally accepted rules regarding road traffic;

**WHEREAS,** the ratification of this Convention is significant in ensuring a smooth and efficient cross-border road traffic for Ethiopia as our country is landlocked; and enhances the road safety standards of our country thereby mitigating the damages ensuing from road traffic accidents;

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ባካሄደው ፭ኛ ልዩ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የተባበሩት መንግሥታት የመንገድ ትራፊክ ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **<u>የኮንቬንሽኑ መጽደቅ</u>**

የመንገድ ትራፊክን በሚመለከት በኦስትሪያ /ቪየና/ ከተማ እ.ኤ.አ. በህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፷፰ ፀድቆ በተባበሩት መንግስታት ስራ ላይ የዋለው የቪየና ኮንቬንሽን በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **<u>የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የትራንስፖርት ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር፣ መንግሥታዊ ከሆኑ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ይህን ኮንቬንሽን በስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ስልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፬. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሀምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 5th special session held on 7th day of July, 2021;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Article (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is proclaimed as follows.

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "Proclamation for the Ratification of United Nations Convention on Road Traffic No.1260 /2021".

2. **<u>Ratification of the Convention</u>**

The United Nations Convention on Road Traffic adopted on the 8th of November, 1968 in Austria, /Vienna/ is hereby ratified.

3. **<u>Powers of the Ministry of Transport</u>**

The Ministry of Transport is hereby vested with the power to enforce the application of the Convention in collaboration with federal, regional, city administration, governmental and non-governmental organs.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force from the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa on this 15th Day of July, 2021**

**SAHLEWORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRTIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**